# ባለፉት 27 ዓመታት የትግራይ ተወላጆች የያዙትን የፖለቲካ አቋምና ምክንያቶቹ

ወልዳአብ ድንቡ **(April 13/2018 -ሚያዚያ 4/8/2010)**

**ይህ ጽሁፍ ባለፉት 25 ዓመታት የትግራይ ............................በሚል እ.ኤ.አ በ16/12/2016 ለአንባቢያን አደባባይ ወጥቷል። ዶ/አብይ ለጠቅላይ ምኒስተርነት መመረጥ ዋዜማ ድረስ ፤ "በኢትዮጵያ የበላይነት የነገሠው ትግራይዊነት ወይስ ህወሃታዊነት" በሚል በተለያዩ ሚዲያ ዘርፎች ለአራት ሳምንታት ያህል የጦፈ ክርክር (boiling dispute) በመደረግ ላይ እያለ አሸናፊውና ተሸናፊውን ሳይታወቅ ወደ ዶ/አብይ ሹመት አውንታዊና አሉታዊ ፋይዳ ታይታና  ክርክር ተዞረ/ተገባ። <1> በዚህ ጽሐፍ ላይ አንዳንድ ተዛማጅ ነጥቦች ስለታከለበት <2> ህወሃት/ወያኔ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከገዛ እና ትግሬዎች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ተሰልፈው የህወሃት/ወያኔ ግፍ እስካልተቃወሙ ክርክሩን መቀጠሉን ስለማይቀር፤ ይህ ጽሁፍ ለክርክሩ አስተዋጾ ያደርግ ይሆናል ብለን በማሰብ አደባባ እንዲወጣ ፈለግን ።**

**ጽሁፉ ከዚህ ይጀምራል**

የጥንታውያኖቻችን ዘመን ፣የቅም-ያቶቻችን ዘመን ፣ያያቶቻችን ዘመን ፣ያባቶቻችን ዘመን እያልን ያ ትውልድ ያፈራው ማኅበረስብ ዘመን ተደረሰ ። በሁሉንም ዘመን የነበሩትን ቀደምቶቻችን የሚታወሱባቸው ገድሎች እና ቅርሶች (ለጋሲ) አልዋቸው ። ስለቅድመ ወያኔ/ህወሃት ጅግኖቻችን አበይት ወይም ወርቃማው ትውስታችን የሚሆነው ፣አገራችን ኢትዮጵያ በመሳፍንት አገዛዝ በነበረበት ዘመንም ሆነ በማእከላዊ መንግሥት መተዳደር ከተጀመረ በኋላ የፖለቲካ ሥልጣንና የምጣኔ ሃብቷ(economy resources) በጨበጡትና ባልጨበጡ ተፎካካሪዮች መካከል  የከረረም ሆነ መለስተኛ ቅራኔዎች ቢኖርዋቸውም ፣በጋራ የኢትዮጵያ 'ሉዓላዊነትና ዳርድንበር' ሲያስከብሩ መኖራቸውን ነው ።

ያያቶቻችን ዘመን የሚተወሰው በአደዋ ጦርነት ሲሆን ያባቶቻችን ዘመን የሚተወሰው በማይጨው ጦርነት ወይም ከሁለተኛው የጣሊያን ወራሪ ሠራዊትጋር በተደረገ ጦርነት ነው። የእኔም አባት ከሁለተኛው የጣሊያን ሠራዊት ጋር ከተፋለሙት ጀገኖች አባቶቻችን አንዱ ነበር።  የእኔ ትውልድ የሚተወሰው 'ያ ትውልድ' በሚል ነው  ። ስለያ ትውልድ ቀናኢ ታሪክ በተለያዩ ጸሃፊዮች የተዳሰሰና አድማሰ ሰፊ ስለሆነ ማንጸባረቅ ከምፈልገው  ጉዳይ ጋር ለማገናኘት ያህል ቆንጸል አድርጌ አቀርበዋለሁ ። ማለት፤

> <2> አሁን ኢትዮጵያን መግዛት ብቻ ሳይሆን መልክአ ምድሯን እንድቅርጫ ሥጋ ለመሸንሸን፣ንዑስ ሕዝቧበሌላ ንዑስ ሕዝቧላይ ለማስነሳት ለ27 ዓመታት እየዳከሩ ያሉትን መንጋ ህዋሃቶችን <2>በሜኤሶንና በኢሕአፓ መካከል በተፈጠረው  የፖለቲካ መስመር ልዩነት ምክንያት የተፈጠሩትን አሳዛኝ ይሁንታዎችን ሳላካትት፤

ያ ትውልድ  የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበራዊ ፍትኅ አጣ ማለት (በድኅነት ተጎሳቆለ ፣በበሽታ ተጠቃ ፣በመኖርያ ቤት እጦት ምክንያት በረንዳ አዳሪዩ በዛ ፣ ትምህርት ለሰፊው ሕዝብ አልተዳረሰም ፣ ገበሬው አርሶ የሚኖርበት መሬት አላገኘም፣በኢ-ሃቅ ዳኝነት ተቸገረ) ፣አገራችን ዘመኑ ከሚፈቅደው የዕድገት ጥበቦች ወደኋላ ቀርቷል ፣ የብሄር

ብሄረሰቦች- (ቋንቋዎች፣ ባህሎች እና የእምነት እሴቶች በእኩልነት አልተሰተናገዱም) ፤የእነዚህ ሁሉ ምክንያት የመልካም /የዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እጦት ነው በማለት፡-

በጎሳ ፤በቋንቋ ፤በባህል፤በሃይማኖት በጾታ፤በርዕዮት ዓለም ፤በመደብ ፤በጎጥ፣ በሞያ ወዘተ..ሳይከፋፈል ለሁለገብ ለውጥ ታገለ ።

የሃይለሥላሤ ፈላጭ ቆራጭ ንጉሣዊ እና የደርግ ፋሽስታዊ ሥርዓቶችን ለማስከበር/ለማስቀጠል ከሰለጠኑትን ፖሊስዎች፤ፈጥኖ ደራሾች፣ ጸረ-ሕዝቦችና ነፍስ ገዳዮች ጋር ግብግብ ገጥሞ የሕይወት መሰዋዕት ከፍሎዋል(ያ ትውልድ) ። ያ ትውልድ ከግለኝነት የነጻ (selfless) ትውልድ ነበር ። ያ ትውልድ በአገሩ፣ በሕዝቡ ፣ በታሪኩ ፣ በማንነቱ ወዘተ..ኩራትና ፍቅር የታነጸ ትውልድ ነበር። ያ ትውልድ ከአንድ እናት ማኅጸን የተወለደ ወንድምና እህት ይመስል ነበር ።

አሁን በፀረ- ኢትዮጵያና በፀረ-የኢትዮጵያዊነት መተክልና መርሃግብር ተሰልፈው የሚገዙንን ቁንጮ የወያኔ/የኅወሃት ባንዳዎች የዚያ ትውልድ ትግል አጋር ነበሩ/አልነበሩም ለማለት የሚያስችል ጭብጥ ማስረጃ ባይኖረኝም ፤አልነበሩም ማለትን እመርጣለሁ። ምክንያቱም እነዚህ ባንዳዎች በዚያን ግዜ-በዩኒቨርስቲ፤በኮሌጆች፤በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ ቅጥር ግቢዮችና በየትግሬዎች ቡና ቤቶች ውስጥ በስውር እየተሰበሰቡ ስለትግራይን መገንጠል ይወያዩና ይደራጁ ነበር ።አብዛኞቹ በአባታቸው ውይም በአያታቸው ባንዳዎች ቢሆኑም ፡-የቀኝ አዝማች፤የግራዝማች፤የፊታውራሪ ወዘተ..ልጆች ናቸው። ሃይለሥላሴ ሥልጣናቸውን ይዳፈራል ብለው የሚፈሩት ከአገር ወዳድ ጀግና አርበኞች የበለጠ ባንዳዎችን ነበር። ስለሆነም ግራዝማች፤ቀኝ አዝማች ፤ፊታውራሪ ፤ባራምባራስ ወዘተ.. እያለ ይሾማቸው ነበር። ከጭቁኑ አርሶ አደር፤ከጭቁኑ ላባደረ፤ከጭቁኑ ነጋዴ ወዘተ..የሚሰበሰበው ግብር ለእነዛ ሹማምንት ድጎማ ይሰጥ ነበር።

ከላይ ያስጨበጥኩት እውነታ እንዳለ ሆኖ ፡-አነስተኛ ፤መካከለኛና ከባድ ክብደት የነበራቸው የትግራይ ተወላጆች ከያ ትውልድ ጋር ሁነው ታግለዋል ። ከባድ ክብደት ከነበራቸውና በቀንደኝነት ከያ ትውልድ ጋር ከታገሉት ውስጥ - ጥላሁን ግዛው ፤ብርሃነመስቀል ረዳ ፤ማርቆስ ሃጎስ ፣ ተስፋዬ ደበሳይ ፣ ዘሩ ክሸን ወዘተ.. ይገኙበታል ።

ባለፉት 27 ዓመታት የትግራይ ተወላጆች የያዙትን የፖለቲካ አቋም ከላይ ከገለጽኳቸው ቀደምቶቻችንም ሆነ ከያ ትውልድ ታሪክና ገድል ፍጹም በተቃራኒዩ ስለመሆኑ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን አንድ ሁለት ብሎ ማስረጃ ማቅረብ ባያስፈልግም ፤ እውነቱን ለሚክዱ የትግራይ ተውላጆች እጅግ በርካታ ከሆኑ ማስረጃዎች ጥቂቶችን እጠቁምላቸዋለሁ ። ከዚህ በመቀጠል የምጠቁማቸው ማስረጃዎች በባዕዳን አገራት የሚኖሩ የትግራይ ተውላጆችን ይሁ ንታ/ድርጊቶች እንጂ በወያኔ የአፓርታይድ ሥርዓት ምክንያት ባገር ቤት ለ27 ዓመታት ትግ ራይ ባልሆኑ ኢትዮጵያውያን ላይ የተፈጸሙትንና በመፈጸም ላይ ያሉትን ሁለገብ ግፎችና ጥቃቶችን አያካትትም ። ይኸውም ፡-

I.ወያኔ/ህወሃት የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዢ መሆን በጀመረ ማግሥት የትግራይ ተወላጆች በባ ዕዳን አገራት በኢትዮጵያዊነት ከተደራጁትን ማኅበሮች/ኮምኒቴዎች ተለይተው -ትግሬዎችን ብቻ ያቀፈ ኮምኒቲ/ዮች መመሥርት ጀመሩ/መሥርቷል

2.በኢትዮጵያዊነት ተመሥርተው ኢትዮጵያውያንን በዕኩልነት ይገለገሉባቸው የነበሩትን ቤተክርስቲናትና መስጊዶች ለማዳከም ፤ (1) ትግሬዎችን ብቻ ያቀፈ (2) ለወያኔ ያደሩ ሆዳም ኢትዮጵያውያንን ያቀፈ/ፉ ቤተክርስቲያናትና መስጊዶች ማደራጀት ጀመሩ/አድራጁ

3. በቅድመ ወያኔ በኢትዮጵያዊነት በጋራ ተሳትፎ እናከብራቸው የነበሩትን የዘመን መለወጫ፣ የገና ፣የፋሲካ ፣የኢድ አልጢር ፣የሮመዳን ወዘተ.. አውደ በዓሎቻችንና ወግ ማዕረጎቻችንን እኛና እነሱ በሚል በትግሬነትና በትግራይ ተወላልጅነት ስብስብ ብቻ ማክበር ጀመሩ

4.እኔ በምኖርበት የአውስትራሊያ ግዛቶች/ ስቴቶች አንዱ ዋና ከተማ 2500- 3000 ቁጥር ያላቸው የትግራይ ተወላጆች አሉ/ይኖራሉ ፤ ወያኔ ለ27 ዓመታት በሕዝባችን ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍ ለማውገዝና የወያኔ ሉዑካን አውስትራሊያ በሚጎበኙበት ወቅት ባደረግናቸው የተቃውሞ ሰልፎች **አንድ የትግራይ ተወላጅ ብቻ በተወሰኑ** ሰልፎች መሳተፉን የተቃውሞ ሰልፍ አዘጋጆች አስተውሎዋል ።

በሰው ቁስል እንጨት መስደት እንደሚባለው የትግራይ ተወላጆች እኛን በመቃወም የወያኔ ግፎች ለማጽደቅና አበጅ ለማለት ሰልፍ ይወጣሉ ። በተለያዩ አጋጣሚዮች ወያኔ አገራችንና ሕዝባችን ከፉኛ የጎዳና የበደለ መሆኑን ሲነገራቸው ለመደባደብ ይቃጣሉ ። ለምን ተደፈርን ብለው ይንጫጫሉ ፣ በወያኔ ላይ የሚነገረው ሁሉ ውሸት ነው (ትግሬ ስለገዛ) ነው በማለት ያዙኝ ልቀቁኝ ይላሉ ።

5.ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ወክለው ወደ ተለያዩ አገሮች የሚላኩትን አምባሳደሮችና ሌሎች ልዕኳን ስለአገር ጉዳይ የሚያወያዩት ትግሬዎች ብቻ በመሰብሰብ ነው ። ይህ ሁሉ ሲሆን በግልም ሆነ በቡድን ልክ አይደለንም ፣አገባብ ያልሆነ ድርጊት ነው የምንሰራው ብሎ የተናገረ ፣ ድምጽ ያሰማ ፣ የጻፈ ወዘተ ትግሬ የለም

**6.እኛ ስናዝን እነሱ ይደሰታሉ ፤እኛ ስናለቅስ እነሱ ይስቃሉ**

**7.በወያኔ የግፍና የሰቆቃ ሥርዓት አንገፍግፏቸው ራሳችውን (ስለሚሰቅሉና ስለሚያቃጥሉ) ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ሲነሳ ጠግቦ/ጠግባ ነው በማለት ይሳለቃ ሉ፤ያሾፋሉ ።**

> **የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳምና ድርጊቱን ያሳዘናቸው ኢትዮጵያውያን ለምን እንደዚህ ያደርጋሉ? እንዴት ጎራ ለይተው ይሰለፋሉ? ምክንያቱ ምን ይሆን? እያሉ-በነጠላም ፣ በጥንድም ፣በቡድንም አዘወትረው ከጠየቁና ከተወያዩ በኋላ፣ ትግሬዎች ጎራ ለይተው የተሰለፉት በሚከተሉት ምክንያቶች እንደሆነ በጉዳዩ የተወያዩ ሁሉ ይስማማሉ (እኔ በምኖርበት አካባቢ) ማለቴ ነው ።**

**II.** **የአገራችንን የፖለቲካ ሥልጣን በእነሱ ጠባብ ዘውግኞች እጅ በመውደቁ ፤**

-የ90 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፡-ሙብት ፣አእምሮ ፣አንድበት፣እጅና እግር መቆጣጠር በመቻላቸው የበላይነት(supremacy)ስለሚሰማቸው

- ቤተሰባቸውም ሆነ እነሱ ወደ አገር ቤት ሲመለሱ አዛዥ እንጂ ታዛዥ እንደማይሆኑ ስለሚያውቁ

- በኢትዮጵያ በሁለገብ የሥልጣን ተዋረድ ዘመዶቻቸው በአንጻራዊ አዛዥነት ማዕረግ እንጂ በታዛዥነት እንደማይሰሩ ስለሚያውቁ

- የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት ምንጮች ፦ማዕድኖች፣ለም አፈሮች፣የወንዞች ውሃ፣ዛፎች፣የዛፍ ግንዶች፣ጥሬ ሃብቶች፣ ኢትዮጵያውያን በላባቸው ያፈሩትን ሃብት ወዘተ.. <The wealth of Ethiop> በሙሉ በእነሱ ጎሳ/ዘውግ እጅ በመውደቁ እና የትግራይ ማልሜያ በመዋላቸው - 104 ሚሊዮኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሬት አልባ በሆነበት፤ በሁሉንም የኢትዮጵያ መልከዓምድር ውስጥና ዙሪያ የሚፈልጉትን ያህል እና የሚፈልጉትን ዓይነት መሬት ስለሚሰጣቸው

-ከአፍሪካ ሚሊየነሮች ቁንጮውን ቦታ የያዙት እነሱ በመሆናቸው

- ጭብጥ ቆሎ ተይዞ ወደ አሻሮ ምጣድ መጠጋት እንደሚባለው ፣ባደጉት ባዕዳን አገሮች በመሥራት ያገኙትን ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ለሥራ ፈትነትና ለጡረታ ከሚከፈላቸው የገቢምንጭ ያጠራቀሙትን ይዘው ወደ አገር ቤት በመሄድ ከወለድ ነጻ በሆነ ብድር ጎንጻዎች/ቪላዎች አሰርተው ወይም ገዝተው ማከራየት ስለቻሉና ስለሚችሉ

- ያለወለድ ከባንክ መበደር የሚያስችል የተለየ መብት ስለተሰጣቸው

-ያለቀረጥ አስመጪና ላኪ የመሆን መብት ስላላቸው

-በፖለቲካ ምክንያት በመንግሥት እንደሚፈለጉ የማስመሰያ (ፌክ) የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ አዘጋጅቶ በመስጠት ወደ ስደት ስለሚላኩ

-ያደጉ አገሮች በሞያም ሆነ ለንግድ ከድሃ አገሮች ወደ አገራቸው ለመውሰድ ያዘጋጁትን መሥፈርቶች (crieteria) የሚያሟሉ ሰነዶች አዘጋጅተው ስለሚሰጧቸው

-ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አደጉ አገሮች ከሚላኩት 95% የትግራይ ተወላጆች በመሆናቸው ወዘተርፈ

## II.ቅኝ ገዢዮች በቅኝ ተገዢዮችን ለማስተዳደር የተጠቀሙበት እኛና እነሱ ፣የበላይነትና የበታችነት፣የማምበርከክና የመምበርከክ የፖለቲካ ሥራዓት/ ርዕዮት አስተምርት ስለተሰጣቸው (for being indoctrinated as us v.s the other , dominant v.s Subordinate Political system/Ideology ) .ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው

ሀ/ የአጼ የሐኒስና የራስ አሉላን ገድል ታሪክ ፣ የአክሱም ሐውልትና የአደዋን ድል ታሪካዊነትና ኩራት ፣ የትግራይ ሕዝብ ገድል፣ ባህል ፣ ቋንቋ ወዘተ..ለሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምኑም አይደለም ፤ ማለት የኢትጵያውያን የገድል ፣የታሪክ ፣የባህል ፣የቋንቋ ፣የሰደቃዓላማ ወዘተ.. እሴቶች ሁሉ ከትግራይ ሕዝብ ጋር እንደማይዛመድ ወይም እንደማይገናኝ

ለ/ ያለፈው ምዕተ ዓመት ባማራ የበላይነት የኢትዮጵያ ቅኝ ተገዢ ነበርን ፤የሚቀጠለው መቶ ዓመት ሥርወ መንግሥቱ ለትግሬዎች ነው

ሐ/ "ከዚህ ከወርቃማ ትግሬ ዘር በመወለዴ እጅግ በጣም እኮራለሁ" መለስ ዜናዊ ። ያ ማለት ከትግራይ እናትና አባት የተወለደ ሁሉ ወርቃማ ነው ፤ኢትዮጵያውያን 'ከብርና ከነሃስ' የተፈ ጠሩ ስለሆኑ በትግሬዎች መገዛት ወይም በትግሬዎች ሥር መተዳደር ተፈጥሮአዊ ግዴታቸው ነው (by nature, Tigireans are the golden race , they are superior to all Ethiopian ethnics or all Ethiopian ethnics are inferior to Tigireans.Therefore,all the inferior Ethiopians should/must be governed by Tigireans)

መ/ መሳርያ ብንሰጣቸውም ድፍረውም ሆነ ችለው ስለማይዋጉን አትሥጉ !

ረ/ ህወሃት ከሌለ የኢትዮጵያ ፍጻሜ ማለት አርማጊዶን ስለሚሆን ፣ይህንን አደጋ/ሪስክ ወስዶ እኛን የሚዳፈር አይኖርም ፤ ከአሁን በኋላ ትግሬዎች እየተተካካን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያ  ንን መግዛት ነው አይዟችሁ!

ሠ/ በጠመንጃ አፈሙዝ ማሸነፍና መሸነፍ የበጎ አድራጎት ኮንትራት አይደለም ፤ለማሸነፍም ሆነ ለመሸነፍ ዋጋ ያስከፍላል ፣ድሮ የቅኝ ተገዢያቸው ነበርን፤አሁን አሸንፈን ቅኛችን አድርገናቸዋል ፤ እንደቅኝ ተገዢዮች ጸጥ ለጥ ብለው ይገዙልን ፤ የቅኞቻችን እሮሮ የሚሰማ ጆሮም ሆነ የሚያዝን ኅሊና ሊኖረን አይገባም  ወዘተ... የሚሉ ናቸው ። ስለሆነም እነኚያ/እነ ሱ በሚሏቸው  ኢትጵያውያን ላይ -ንቀት ፣ጥላቻ ፣ ጭካኔ ፣ቂምና ትምክህት እንዲኖራቸው ተኮትኩቷል/ታንጿል ።

"Dogmatic ideologies remove doubt, but they have a major drawback. They are bound to be false. They can be imposed on society only by repressive methods that stifle free discussion and prevent a better understanding of reality. Such ideologies lead to a closed society…." (Andras Szanto : in What George Orwell didn`t know………,2007). ቀኖናዊ ዕርዮቶች መጠራጠርን ያስወግዳሉ፣ ግራና ቀኝ ሳይታይ ጭፍን እርምጃ ለመውሰድ ይጠቅማሉ ፣በግድ/በጉልበት ሕዝብ ላይ ስለሚጫኑ ሕዝብ ተወያይቶ እውነቱን እንዳያውቅ ይከለክላሉ ፣ ነገር ግን (lies have got short legs) የውሸት እግሮች  አጭር ናቸው እንደሚባለው ፣ቀኖናዊ ርዕዮቶች ዕድሜያቸው አጭር ነው ፤ የውሸት ሥራቸው ፣የውሸት ተልዕኮዋቸው ጠልፎ ይጥላቸዋል ። እንደ እነዚህ ዓይነት ዕርዮቶች  "ዝግ ማኅበረሰብ" ማለት ከአዲስ እውቀት ፣ ከአዲስ አስተሳሰብ የተገደበና ኋላቀር አስተሳሰብ ያለው ማኅበረሰብ ይፈጥራሉ ።

"We usually remember George Orwell for the dangers he foretold about the effective use of propaganda, through which war becomes peace, torture becomes love ,ignorance becomes strength ,and despots and demagogues

elevate  euphemism to a high art” : Drew Western, ‘The New Frontier ,The Instruments of Emotion,  in Andras Szanto). ጆርጅ ዎርዌል ስለመጻኢ የረቀቀ  የፕሮፓጋንዳ አደገኛነት ‘የተነበየውን’ ሁሌ እናስታውሳለን ፣ **ጦርነት እንደ ሰላም ፣ሰቆቃ እንደ ፍቅር ፤ድንቁርና እንደ ጥንካሬ ወዘተርፈ አድርጎ መስበክ የወደፊት ፕሮፓጋንዳ** እንደሚሆኑ ፣  አንድ ለገሰ ዜናዊ ዓይነት አምባገነኖችና አስመሣይ ሕዝባዊ መሪዮች (populist leaders) ወደ ሥልጣን ለመውጣትና ሥልጣናቸውን ለማራዘም (euphemism) ማለት በማር የተጠቀለለ ኮሶ ወይም መርዝ ባህሪ ባላቸው ስሜት ቀስቃሽ፣ ጣፋጭ ቃላትና ሃረጎች ወደ ከፍተኛ ጥበብና ተወኔትነትን አሳድገው እንደሚጠቀሙ ተንቢዮ ነበር ማለት ይመስለኛል ።

## III.የንቃተ-ኅሊና  ዝቅተኝነት

**ትግሬዎች ከላይ ጆርጅ ኦርዌል <George Orwell>**  ለተነበየው ዓይነት ፕሮፓጋንዳ ተጋልጠዋል ፤በንደዚ ዓይነት ፕሮፓጋንዳ  ተጠልፎዋል፣ በንደዚህ ዓይነት እውሸት አእምሯቸው ታጥቧል። በሳይኮፓቲኩ <psychopathic> መለስ ዜናዊና ሌሎች ቁንጮ ወያኔዎች የስብኳቸውን ሁሉ ፡- ሳያኙኩ ፤ሳያጣጥሙ፤ሳይጠይቁ፣ ግራና ቀኝ ሳያዩ እንደወረደ ውጠውታል።   **Psychopathic**, sometimes considered synonymous with sociopathy, is traditionally defined as a personality disorder[1] characterized by persistent antisocial behavior, impaired empathy, impaired remorse, bold, disinhibited, and egotistical traits. Different conceptions of psychopathy have been used throughout history. These conceptions are only partly overlapping and may sometimes be contradictory (source:wikipedia)

IV. ፈጣን የመጓጓዣና የመገናኛ ጥበብ/ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እድገት ምክንያት የዓለም ማኅበረስብ ድንበረየለሽ በሆነበት ፣ ብሄራዊ/አገራዊ ማኅበረሰብ ከዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ በእውቀት ፣ በንግድ ፣በምጣኔ ሃብት ፣ በጋብቻ ፣በማኅበራዊ ኑሮ ፣ በሃዘን ፣በደስታ ወዘተርፈ በተገናኘበት 21ኛው መቶ ክ/ዘመን ፣ ጨቅላ ግልገሎቿን (bunnies) አውሬዎች እንዳይበሉባት ጉድጓድ ውስጥ አስቀምጣ ፤ጉድጓዱን ጫፍ ላይ ሆና ዘብ እንደምትጠብቅ  እናት ሚዳቆ ፤ በጎሳ ዙሪያ ከመኮልኮል አስተሳሰብ (from primordial thinking) ንቃተ ኅሊና ያለመውጣት/ያለመላቀቅ  ።

ትምኅርት ቤት በመሄድ ፣ በመማር ፣ በማንበብና በመጻፍ  ብቻ ‘ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና’ አይሸመትም/ አይዳበርም ። የተለያየ ባህል ፣ ቋንቋ  ፣ልማድ ፣ ልምድ ፣እውቀት ፣እምነት ወዘተ..ካላቸው አገር በቀልና ባዕዳን ግለሰቦች ፣ ቡድኖች ፣ ኮምኒቲ/ማኅበረሰብ  ወዘተ.. ጋር አብሮ በመብላት ፣ በመጠጣት ፣በመጫወት ፣በመወያየት ነው ንቃተ-ኅሊና የሚዳብረው (through integrating and interacting with people from divers socio-cultural,socio-lingual, socio-political etc background) ።  ከላይ **እንደተገለጸችው**

**እናት ሚዳቆ እነዚያ የሚልዋቸውን ስለሚጠራጠሩ፣ስለሚፈሩና ስለሚጠሉ በጎሳ ስንሰለት ተሳስረውና በጎሳ አጥር ታጥረው ይኖራሉ ፤ ስለሆነም ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ንቃታቸው ዝቅተኛ ነው ።**

**በመሆኑም ከአገር ውጭ ያሉትም ሆኑ የአገር ቤት የትግራይ ተውላጆች ላለፉት 27 ዓመታት ህወሃት/ወያኔን አቅፈውና ደግፈው ከተጓዙበት ከላይ ከተጠቀሱት በርካታ ምክንያቶች በተጨማሪ ፣ንቃተ ኅሊና ስለሚያንሳቸውም ነው ይላሉ (በአካባቢዬ በዚህ ነጥብ ዙሪያ የሚወያዩ ኢትዮጵያውያን)። ስለወያኔ/ህወሃት ሁለገብ ግፍና ጥፋት በጥቂት ቃላት ሲገልጹ "ወያኔዎች ኢትዮጵያውያንን አርዶ ከከብት *ሥጋ ጋር* ደባልቆ ኤክስፖርት <export> ማድረግ አልጀመረም እንጂ ሌላ ምን ቀረው" ይላሉ፣** እኔ ጻፍልኝ ያሉኝን ጻፍኩ እንጂ እይታውና ግምገማው የእነሱ ነው ።